የ ድ ሬ ዳ ዋ  አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ ጣ

# D I R E  N E G A R I T G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

፫ኛ ዓመት ቁጥር ፸፭
ድሬዳዋ ግንቦት ፲ ቀን ፳፻፲፭

በድሬዳዋ አስተዳደር
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 75
DIRE DAWA may 18th, 2023

## አዋጅ ቁጥር ፸፭/፳፻፲፭

**<u>የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤትንና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ብዛት እና የምርጫ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ አዋጅ</u>**

የድሬዳዋ አስተዳደር የሥልጣን አካላት አደረጃጀት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ መሠረት በማዕከልና በቀበሌ የሥልጣን አካላት በሁለት እርከን የተከፈለ በመሆኑ፤

በዚህ አደረጃጀት መሠረት ነዋሪዎች በቀጥታ እና በነፃነት በመረጧቸው ተወካዮች አማካይነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ሥልጣናቸውን በተግባር ላይ የሚያውሉበትን ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No,75/2023

**<u>A proclamation for the Determination of number of members of the Dire Dawa Administration council and the kebele Administration council and the election process.</u>**

**WHEREAS,** the organization of the authorities of the Dire Dawa Administration is divided in to two stratum according to the Dire Dawa Administration charter proclamation No, 416 /2004;

**WHEREAS,** it is necessary to create a situation where residents can exercise their power to govern themselves through directly and freely elected representatives.

በዚሁ መሠረትም በአስተዳደሩ ሊኖር የሚችለውን የምርጫ ክልል ብዛት፣ የቀበሌ አስተዳደሮችን ቁጥር፣ የህዝብ አወካከልና የአመራረጥ ሁኔታ በተመለከተ የድረዳዋ አስተዳደር ቻርተርንና የአገሪቱን የምርጫ ህግ መሠረት በማድረግ በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ -ምግባር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፪/፳፻፲፩ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንዲሁም በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪)(ነ) መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤትንና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ብዛትና የምርጫ ሁኔታን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፳፻፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

**WHEREAS,** based on this it is necessary to determine by law the number of constituencies under the Administration, the number of kebele administrations, public representation and the state of election in accordance with the Dire Dawa administration charter and the country's election law;

**NOW**, **THEREFORE,** in accordance with Article 7(4) and Article 8(2) of Ethiopian electoral, political parties Registration and election's code of conduct proclamation No, 1162/2019 and Article 12(2) (N) of the Dire Dawa Administration charter proclamation No 416/2004,The Dire Dawa Administration council proclaimed as follows.

## Part one
## General provisions

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Determination of the number of members of the Dire Dawa administration council and the kebele administration council and the election process" proclamation No.75/2023.

### 2. Definitions

In this proclamation, unless the context requires otherwise;

፩. **"ቻርተር"** ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮ ነው፤
፪. **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓሪቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ- ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/፳፻፲፩ ነው፤
፫. **"አስተዳደር"** ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፤
፬. **"አስተዳደር ምክር ቤት"** ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት ነው፤
፭. **"የቀበሌ ምክር ቤት"** ማለት በድሬዳዋ አስተዳደር በቀበሌ ደረጃ ያለ ምክር ቤት ነው፤
፮. **"ቀበሌ"** ማለት በከተማ እና በገጠር የሚገኝ የአስተዳደሩ ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው።

## ክፍል ሁለት
## ስለ ምርጫ ክልል እና የቀበሌዎች ብዛት

### ፫. የምርጫ ክልሎች ብዛት

፩. ለምክር ቤቶቹ የሚመረጡትን አባላት ቁጥርና የመራጩን ብዛት መሠረት ያደረገ ተመጣኝ የምርጫ ክልሎች በአስተዳደሩ እንዲቋቋም ይደረጋል።
፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት በአስተዳደሩ በከተማና በገጠር የሚቋቋሙት የምርጫ ክልሎች ብዛት 2 ይሆና

1. "charter" means the Dire Dawa Administration charter proclamation No, 416/2004;
2. "proclamation" means the Ethiopian electoral, political parties registration and election's code of conduct proclamation No, 1162/2019;
3. "Administration" means the Dire Dawa Administration
4. "Administration council " means the Dire Dawa Administration council;
5. "Kebele council " means a council at the kebele level in Dire Dawa Administration;
6. "Kebele" means the second administrative stratum of the Administration in urban and rural areas.

## Part Two
## The constituency and the number of kebeles

### 3. The number of constituency

1. Based on the number of members to be elected to the councils and the number of voters proportional constituency
2. According to sub- article (1) of this article the number of constituency established by the administration in urban and rural area shall be two.

**፬. ምርጫ ስለሚካሄድባቸው የቀበሌ አስተዳደሮች ብዛት**

፩.በአስተዳደሩ በከተማ የሚኖሩ የቀበሌ አስተዳደር ቁጥር ለምርጫው ሲባል ብቻ የቀድሞውን 25 ቀበሌ መሠረት ያደረገ ሲሆን ዝርዝሩም እንደሚከተለው ይሆናል።

ሀ. ቀበሌ 1 የቀድሞውን 1 ቀበሌ (ቀበሌ 25) ይወክላል፥

ለ. ቀበሌ 2 የቀድሞውን 3 ቀበሌ (ቀበሌ 01, 02 እና ቀበሌ 24) ይወክላል፥

ሐ. ቀበሌ 3 የቀድሞውን 3 ቀበሌ (ቀበሌ 03, 04 እና ቀበሌ 05) ይወክላል፥

መ. ቀበሌ 4 የቀድሞውን 3 ቀበሌ (ቀበሌ 06, 07 እና ቀበሌ 08) ይወክላል፥

ሠ. ቀበሌ 5 የቀድሞውን 4 ቀበሌ (ቀበሌ 09, 10, 11 እና ቀበሌ 12) ይወክላል፥

ረ. ቀበሌ 6 የቀድሞውን 4 ቀበሌ (ቀበሌ13, 14, 15 እና ቀበሌ 16) ይወክላል፥

ሰ. ቀበሌ 7 የቀድሞውን 3 ቀበሌ (ቀበሌ17, 18 እና ቀበሌ 21) ይወክላል፥

**4. The number of kebele administration for which eleation are held**

1. For the purpose of election, the number of kebeles in urban area is based on the previous 25 kebeles, the details shall be as follow;

a. Kebele represent the former kebele 25

b. Kebele 2 represent the former kebele 01,02 and 24;

c. Kebele 3 represent the former kebele 03,04,and 05;

d. Keble 4 represent the former kebele 06,07, and 08;

e. Kebele 5 represent the Former keble 09,10,11 and 12;

f. Keble 6 represent the formedr kebele 13,14,15 and 16;

g. Kebele 7 represent the former kebele 17,18, and 21;

ሸ. ቀበሌ 8 የቀድሞውን 2 ቀበሌ (ቀበሌ 19, እና ቀበሌ 20) ይወክላል፡

ቀ. ቀበሌ 9 የቀድሞውን 2 ቀበሌ (ቀበሌ 22 እና ቀበሌ 23) ይወክላል፡

፪.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት 25 ምርጫ የሚካሄድባቸው የከተማ ቀበሌዎች ይኖራሉ።

፫.በገጠር ምርጫ የሚካሄድባቸው ቀበሌዎች ብዛት 38 ይሆናል።

፬.በዚህ አንቀጽ መሰረት በአጠቃላይ ምርጫ የሚካሄድባቸው የአስተዳደሩ ቀበሌዎች ብዛት ፷፫ ይሆናል።

## ክፍል ሦስት
## ስለ አስተዳደር ምክር ቤት እና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ምርጫ

### ፭ የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ምርጫ፣ ብዛት እና አወካከል

1. የአስተዳደር ምክርቤት አባላት ምርጫ የሚካሄደው በአስተዳደሩ ስር የሚገኙ ቀበሌዎችን መሰረት በማድረግ ነው።

h. Kebele 8 represent the former kebele 19 and 20;

i. Kebele 9 represent the former kebele 22 and 23,

2. According to sub- article (1) of this article there shall be 25 urban kebeles where election held by the Administration.
3. The number of kebeltes that that be held in rural eleation shall be 38.
4. According to this article, the number of administration kebeles for which election be held shall be 63.

## Part three
## Election of the Administration council and kebele Administration council

### 5. Election of the Administration council and kebele Administration council

1. The election of members of the administrative council is done based on the kebele under the Administration

፪.ከእያንዳንዱ ቀበሌ የሚመረጠው የአስተዳደር ምክር ቤት ተወካይ አባላት ብዛት ፫ ይሆናል።

፫.የአስተዳደሩ ምክር ቤት አባላት ቁጥር 189 ይሆናል።

፬.አንድ የአስተዳደር ምክር ቤት አባል የተመረጠበትን የቀበሌ ነዋሪዎች ይወክላል።

**፮. ስለ አስተዳደሩ ምክር ቤት አወቃቀር፤**

የአስተዳደር ምክር ቤት በከተማ ቀበሌዎች እና በገጠር ቀበሌዎች ተማራጮች የተዋቀረ ምክር ቤት ነው።

**፯. ስለ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ምርጫና ብዛት**

፩. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ምርጫ የሚካሄደው የቀበሌውን ነዋሪዎች መሰረት በማድረግ ነው።

፪. አንድ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባል የተመረጠበትን የቀበሌ ነዋሪዎች ይወክላል።

፫. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ብዛት 100(አንድ መቶ) ይሆናል።

**፰ ስለ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አመራረጥ**

2. The Number of representative members of the Administration council elected from each kebele shall be 3.

3. The member of the Administration council member is 189.
4. The member of the Administration council represents the residents of the kebele form which he was elected.

**6. Structure of the Administration council**

The Administrative council is made up of elected representatives from the urban and rural kebeles,

**7. Election and number of members of the Kebele administration council**

1. The election of members of the kebele council is conducted based on the residents of the kebele.
2. The members of the Kebele council represents the residents of the Kebele from which he was elected.
3. The number of members of the Kebele council shall be 100.

**8. Election of the kebele Administrative council.**

፩.የቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ህዝብ የሚመረጡ ይሆናል፡፡

፪.የቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ምርጫ ነፃ ፣ ቀጥተኛ እና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ስርዓት ይፈፀማል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፱ የምክር ቤት አባላት ቁጥርን ስለመቀየር

፩. የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ እና ፯ ድንጋጌ ቢኖርም የአስተዳደሩ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምክር ቤቱን አባላት ቁጥር ሊቀየር ይችላል።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአስተዳደሩ ምክር ቤት የአባላት ቁጥሩን ለመቀየር የሚሰጠው ውሳኔ ከዕጩዎች የምዝገባ ሰሌዳ ስድስት ወር አስቀድሞ መሆን ይኖርበታል።

### ፲.የተሻሩና የፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች

፩. የድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌ ምክር ቤት አባላትን ብዛት ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፳፬/፪ ሺህ ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

1. Members of kebele administration council shall be directly elected byte the residents of kebele.
2. The election of Kebele administrative council members is done in a free, direct and secret voting system.

## PART FOUR

## Miscellaneous provisions

### 9. Changing the number of council members

1. Notwithstanding the provisions of Articles 6 and 7 of this proclamation, the administrative council may change the number of members of the council when it deems it necessary.
2. Without prejudice to the provision of sub-article (1) of this article, the decision of the administrative council to change the number of members should be six months before the registration of candidates.

### 10. Repealed and inapplicable laws.

1. The determination of number of members of Dire Dawa Administration Kebele council proclamation no 24/2007 here by repealed.

፪. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ መመሪያና ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## ፲፩ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአስተዳደሩ ድሬ ነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ድሬዳዋ ግንቦት ፲ ቀን ፳፻፲፭**

**ከድር ጁሃር**

**የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ**

2. Any proclamation, regulation, directives or practice which are inconsistent with this proclamation shall have no effect on matters provided in this proclamation.

## 11. Effective date

This proclamation shall come into force up on the date of publication in the Dire Negart Gazeta.

**Done at Dire Dawa, on this may 18th day of , 2023**

**KedirJuhar**

**Mayor of Dire Dawa Administration**